በቅዱስ ዮሐንስ ጠበል ከሆዷ ወፍ የወጣላት እሳት

በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በደብረ ወልደ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንስ እና በመካነ ጎለጎታ ቅድስት ማርያም ጠበል ስሞኑን ከእንዲት እሳት ከሆዷ ጥቁር ወፍ ወጣላት። በክርስትና ስሟ መንበረ ማርያም ተብላ የምትጠራው እሳት ለ20 ዓመታት ያህል በሆድ ሕመማት ስትሰቃይ መቆየቷን የምትናገረው መንበረ ማርያም፤ ስቃይዋን በዘመናዊው ሕክምና ለማስታገስ ያልሔደችበት ቦታና ያልወሰደችው መድኃኒት የለም። ይሁንና የምትወሰደው ሕክምና ለጊዜው ስቃይዋን ከማስታገስ በስተቀር ከሕመሟ ልትድን ባለመቻሏ ከዚህ በኋላ ይግደለኝ እንጂ ሕክም ናም ሆነ መድኃኒት መጠቀም የለብኝም፤ ብላ ጠበል ለመጠመቅ እንደ ወሰነች ትናገራለች። በውሳኔዋም መሠ ረት ወደ ወልደ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንስ ቤተክርስቲያን ጠበል በመሄድ ስትጠመቅ በላይዋ ላይ የሰፈሩ 681 አጋንንት እንዳሉ በላይዋ ላይ ያደሩት የሰይጣን ሠራዊት ለፍልፎ በጥቁር ወፍ እምሳል ከሆዷ ውስጥ ሊወጣላት ችሏል።

ምእመናን በዕለቱ ከሆዷ ውስጥ በትውከትነት እንደ ጥይት ተወርውሮ የወጣውን ጥቁር ወፍ ከነሕይወቱ በማየት በቪዲዮ በመቅረጽ የእግዚአብሔርን ድንቅ ተአምር እንደ መስከሩ ተገልጿል።

የሰምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ስምቶ ይህንኑ ወፍ የወጣላትን መን በረ ማርያምንና ያጠመቋትን አባት ሊቀ ትጉኃን ሰሙር አሐዱን በማነጋገር ድርጊቱ እንዴትና ምን ይመስል እንደነበር በሰፊው ዘግቧል።





እግዚአብሔር ሥራው ድንቅ ነው፤ ተዓምሩ ዕፁብ ነው፤ ተነግሮ አያልቅም፤ ይህን ሥራውን መመሰከር ደግሞ የእኛ ተግባር ነው። ለረጅም ዓመታት በሕመም ስትሰቃይ የነበረች በሰመ ጥምቀቷ መንበረ ማርያም የተባለች ወጣት የእግዚአብሔርን የድንቅ ሥራው መገለጫ ሆናለች።

ለዚህች እህት እግዚአብሔር ያደረገላት ገቢረ ተአምር ሲሰሙት ለጆሮ የሚኩበድ፤ እንዲሁም በወቅቱ ድር ጊቱ ሲፈጸም የተመለከቱ ምእመናንን ሁሉ ያሰደመመ ነበር። «ማን ያርዳ የቀበረ፤ ማን ይናገር የነበረ» ነውና ሥረ መሠረቱ ምን፣ እንዴትና መቼ ሆነ? የሚለውን ጉዳይ እሷው ባለታሪኳ እንዲህ ትተርክልናለች።

«ያመኝ የነበረው ገና የአራት ዓመት ልጅ እያለሁ እስቃይ ነበር። ለምሳሌ የራስ ምታት፣ ነሰር፣ የሆድ ቁርጠት፣ የእንጀት ኢንፌክሽን ወዘተ እየተባለ በመታመም ሁልጊዜ ሐኪም ቤት እመላለስ ነበር። እናቴ እንደ ነገረችኝ የሕመሙ መነሻ ወተት ነው። «ወተት ጠጥተሽ የእንጀት ኢንፌክሽን ያዘሽ» ያለችኝ እናቴ በየክሊኒኩ እየወሰደችኝ ስታሰመረምረኝ መድኃኒት እንደሚያዘልኝ አጫውታኛለች። ራሴን ማወቅ ስጀምር ትምህርት ቤት ገብቼ ስማር ሆዴን ያመኛል። በተለይ በበጋ ወራት ተምሬ ሁለት ወር ክረምት በሚሆንበት ወቅት ክፉኛ ያመኛል» ስትል ተናግራለች።

መንበረ ማርያም በሕመሟ መጥናት ብዙ ጊዜ ሐኪም ቤትና ክሊኒክ ተመላልሳ እንደታከመች ገልጻል ናለች። ነገር ግን ጠበልሰ አልሞከረች ይሆን? የሚለው ጥያቄ አጫረብንና ጠየቅናት፤ እርሷም ሰትመልሰ «በዚያን ወቅት ቤተሰቦቼ የሚያሰቡት ሐኪም ቤት የሚባለውን እንጂ ጠበልን አልነበረም። እኔም ቢሆን በወ ቅቱ ጠበልን አላሰብኩትም፤ ብቻ ሐኪም ቤት ሔጄ የተለያየ መድኃኒት ይታዘዝልኛል እወሰዳለሁ። ለጊዜው ያሰታግሥልኛል፤ ጨርሶ ግን ሊያድነኝ አልቻለም። ይባሰ ብሎ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ወሰጄ ጥሩ ውጤት በማምጣት አራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ገብቼ የመጀመሪያ ዓመት መማር ሰጀምር በሽታው ክፉኛ አሰቃየኝ። ያሰጨንቀኛል፣ ከፍተኛ የራሰ ምታት ሕመም ይሰማኛል፤ ማጥናት አልችልም ነበር። የሴሚሰተር ፈተና ደርሶ ሁለት ሳምንት ሲቀረው አንደኛው ዐይኔ ውሰጡ ሲቆሰል ሌላኛው ዕንባ ማፍሰሰ ጀመረ። ዕንባው ያለምንም ማቋረጥ ለ24 ሰዓታት ይወርዳል። ቤተሰቦቼ ሁኔታው አላምር ቢላቸው ወደ እንዲት ታዋቂ የዐይን ሐኪም ወሰዱኝ። እሷም 'በሕይወቴ እንዲህ ዐይነት ነገር ዐይቼ አላውቅም፤ ዐይኗ ውሰጥ ቁሰል አለና የመታት ነገር አለ ወይ?' ብላ ጠየቀች። ይሁንና ቤተሰቦቼም ሆኑ እኔ ምንም ነገር የመታኝ ነገር እንደሌለ ለዶክተሯ ነገርናት። በየሰዓቱ የሚደረግ ጠብታ አዛልኝ ለጊዜው ተሻለኝ። የከፍተኛ ትምህርቴን ግን ሳልማር ለሁለት ዓመት ያህል አቋረጥኩ» ትላለች የሕመሙን አሰከፊነት የምትናገረው መንበረ ማርያም።

መንበረ ማርያም እንደገለጸችልን በጤና መታወክ ሳቢያ ለጊዜው ትምህርቷን ብታቋርጥም ለትምህርቷ ያላት ቁጭት ከፍተኛ ሰለነበር በሽታው መጣ ሔድ እያለ ቢያሰቸግራትም ከዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በመግባት ትምህርቷን በሥራ አመራር የትምህ ርት ዘርፍ ለአራት ዓመታት ያህል ተከታትላ በ1996 ዓ.ም በዲግሪ ተመርቃለች።

ይሁንና ሌላ ያላሰበችው ችግር ገጠማት፤ ይህሰ ምን ይሆን? ለዚህም መንበረ ማርያም ሰትናገር «የወር አበባዬ ከመጣበት ጊዜ እንሥቶ አሁን እሰከዳንኩበት ጊዜ ድረሰ በየወሩ በጣም እያመመኝ ክፉኛ ያሰቃየኛል። ሰቃዩን ለማሰታገሻ እያልኩ ፓ¬ራሲታሞል ክኒን በየአራት ሰዓት ልዩነት ሁለት ሁለት ፍሬ በመዋጥ በቀን 10 ፍሬ እወሰድ ነበር። ሐኪም ቤትም ብሔድ የሚሰጡኝ መርፌ ነው። አልሻል አለኝ። የሕክምና ባለሙያዎቹ 'እግብታ ትውለድ፤ ሴቶች እንዲህ ዐይነት ሕመም ሲሰማቸው ይሻላቸዋል ና መውለድ አለብሽ' ብለው አሰተያየት ይሰጡኛል» ትላለች።

እንደ መንበረ ማርያም አገላለጽ ብዙ ጊዜ መድኃኒትም መዋጥ ሌላ ችግር /Side-effect/ ሰላለው መድኃ ኒት መውሰዱን ታቋርጣለች፤ «ኪድጡ ወደ ማጡ» እንዲሉ ይባሰ ብሎ በየወሩ ያማት የነበረው እንደ አዲሰ የማያቋርጥ የማሳፀን ሕመም ይሰማት ጀመር። በዚህን ጊዜም በታወቁ የማሳፀን ሐኪም በመታየት በወር አበባ ሳቢያ የተነሣ በማሳፀኗ ውሰጥ ትናንሽ ዕጢዎች እንዳሉ ይነገራትና የወር አበባዋ ከመምጣቱ በፊት ለአንድ ሳምንትና ከመጣም በኋላ ለአንድ ሳምንት የሚወሰድ ከባድና በጣም ውድ የሆነ መድኃኒት ይታዘዝላ ታል። ይህ የሆነው ከሁለት ዓመት በፊት ነው።

«በዚህን ጊዜ የመጨረሻ ቁርጥ ውሳኔ ወሰንኩ» ትላለች መንበረ ማርያም። «መሞቴ ለማይቀር ነገር ለምን እሰቃያለሁ? በመድኃኒትሰ ለምን እቃጠላለሁ?» በማለት ወደ ጠበል ቦታ ለመሔድ ወሰነች። ጠበሉን እንድትሞክር ያነሣሣትና ምክንያት የሆነቻት ደግሞ ጓደኛዋ እንደሆነች ተናግራለች። «እንድ ጓደኛዬ እንደ እኔ ዓይነት ሕመም ይሰማት ሰለነበር ጸድቃኔ ማርያም ሔዳ ጠበል ጠጥታ እንደዳነች ነገረችኝ። እኔም ጠበል መጠጣትና መጠመቅ እንዳለብኝ መከረችኝ። መድኃኒቱን አቋርጬ ጠበል መጠመቅ ጀመርኩ። እየጸምኩ በተከታታይ ጠበሉን ሰጠጣና ሰጠመቅ በየወሩ የወር አበባዬ ሲመጣ ያመኝ የነበረውን ተወኝ። በመቀጠል ከማሳፀኔ ሥጋ ነገር ተቆርጦ ወጣ። በዚህ ጊዜ ቤተሰቦቼ «እጢው ወጣልሽ» በማለት ተአምር አሉ። ሥጋ መሰል ባዕድ አካል ከወጣልኝ በኋላ ምንም ዓይነት ሰሜት ሳይሰማኝ ጤነኛ ሆንኩ፤

ጠበሉንም አቋረጥኩት» በማለት ገልጻለች።

በዚህ መልኩ ለውጥ ያገኘችበትን ጠበል ሰታቋርጥ ዳግም ሕመሙ ጀመራት። መንበረ ማርያም ትናገራ ለች። «ጠበሉን ለአንድ ዓመት እንዳቋረጥኩ በሽታው በባሰና በሚያሰፈራ መልኩ ተመልሶ መጣ። እንደገና ጠበሉን መጠጣት ጀመርኩ፤ በዚህን ጊዜም ደጋግሞ የሆነ ነገር በሕልሜ ያሳየኛል፤ በሆነ መንገድ ላይ በጣም ጥቁርና ትልቅ ሰውዬ ዝም ብሎ ቆሞ ዐያለሁ፣ ቀጥሎ እኔ ሕፃን ልጅ ታቅፌ ሳመልጥ እሱ ትልቅ ድንጋይ ይዞ እየተከተለ በማሰፈራራት ሲያሯሩጠኝ ዐያለሁ። ይህን ያየሁት በድሮው ቤታችን መገናኛ አካባቢ ነው።

የመንበረ ማርያም ዋናው ታሪክ የሚጀምርው በግንቦት ወር 2001 ዓ.ም ነው። በዕለተ ሰንበት እሑድ ቀን ቅዳሴ እስቀድሳ ሰትመለስ እንደተለመደው የወር አበባ ይታያትና በቃላት ሊገለጽ በማይችል ሁኔታ በጽኑ ትታመማለች። መንበረ ማርያም እንደገለጸችው «መጽሐፈ አርጋኖን ይዛ ከአንዱ ክፍል ወደ አንዱ ክፍል እየተንቆራጠጠች 'ወይኔ! እመቤቴ ኧረ አድኚኝ' እያለች መኝታ ክፍሏ ሆና ሰታጣጥር በድንገት በግድግዳ ላይ የተሰቀለውን የቅዱስ ሚካኤል ሥዕል ታያለች። እያጣጣርኩ በክፍሌ ውስጥ ቁጭ ብዬ ድንገት የተሰቀለውን የቅዱስ ሚካኤል ሥዕል ቀና ብዬ ማየት ሰጀምር የፌዝ ሳቅ መሳቅ ጀመርኩ። በዚህን ጊዜ ራሴን እየለወጠኝ ነው፤ አልፎ አልፎ እንጂ ምን እንደምሠራም አላውቅም፤ መጣሁልህ ይላል። እንደዛር ማጓራት ጀመርኩ፤ አባቴ ሲሰማ ደነገጠ። እሱ እንደነገረኝ ሁለት እጄን ይዞ የቅዱስ ገብርኤል ጠበል እየረጨ 'እንተ ማነህ?' ሲለው 'እባክህ አንተ አታውቀኝም! ዝም ብለህ ነው፤ ተቃጠልኩ ጊዜዬ ሲደርስ የምለቅበት ቀን አለ። እሷን የያዝኩት ከማኅፀን ጀምሮ ያሳደግኳት እኔ ነኝ' በማለት ለፈለፈ። በመቀጠል 'እናቷንም የገደልኩ እኔነኝ' ሲል ራሱን ገለጠ» በማለት መንበረ ማርያም አሰረድታለች። እናቷ በካንሰር ሕመም ምክንያት በ1995 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውንም ገልጣልናለች።

በቅዱስ ሚካኤል ሥዕል ሳቢያ ማንነቱን የገለጠው ሰይጣን እንደያዛት ሰታውቅ፣ የትመጠመቅ እንዳ ለባት ታሰባለች። በመጨረሻም በደብረ ወልደ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ሐዳ ጠበል መጠመቅና መጠጣት ትጀምራለች። በአምሰተኛው ቀን ያደረባት ርኩሰ መንፈስ መለፍለፍ ይጀምራል። በተለይ ሰኔ 10 ቀን 2001 ዓ.ም በዕለተ ረቡዕ ሰትጠመቅ 681 አጋንንት እንደ ሠፈረባት ይለፈልፋል። ብዙ ሰው እንደጨረሰና አሁንም ብዙዎችን እንደያዘ ገልጾ እርሷ ላይ ሲደርስ ግን እንደተጋለጠ ተናግሯል። «ምእመናን እንደነገሩኝ ከሆነ «አንቺ ሰትጮኺ እንደ እንበሳ ነው፤ የሚያሰፈራና ከአንቺ የሚወጣ ድምፅ አይመሰልም ብለውኛል። እኔ ግን በመሐሉ «መድኃኔዓለም መጣ» የሚል ድምፅ ሰማሁ እንጂ ራሴን አላውቅም። መጨረሻ ላይ ራሴን ሳውቅ ከእኔ የወጣውን ጥቁር ወፍ ይዘው አሳዩኝ። አለመንኩም። ሰው እልል እያለ 'አይዞሽ ተነሽ እመቤታችን ከነልጇ የሠራችልሽ ተአምር በጣም ድንቅ ነው። ተነሥተሽ ድንቅ ተአምሯን ትመሰክሪያለሽ' አሉ። ልብሴን ለብሼ ሰወጣ ብዙ ምእመናን ቆሞ በሞባይልና በቪዲዮ የወጣውን ጥቁር ወፍ ይቀርጻል። ከሆዴ የወጣው ትልቅ አፍ ያለው ወፍ ደም ጎርሶ በሕይወት ለተወሰነ ደቂቃ ልቡ ይመታል። እኔ ራሴን አላመንኩም፤ ደስታ አይሉት ሐዘን ተደበላለቀብኝ፣ ሰውነቴ ከላይ እስከታች ይርዳል» ስትል የእግዚአብሔርን ድንቅ ተአምር መሰክራለች።

ሰኔ 10 ቀን ከ681 አጋንንት ውስጥ ሰማኒያው ጥቁር ወፍ ሆኖ ሲወጣ ሰኔ 12 ቀን ሌሎች ቀሪዎቹ በጉንዳን መልክ ወጥተናል ብለው በመለፍለፍ ለቀቁ። በወቅቱም የጠበሉ ቦታ በጉንዳን ተወሮ እንደነበር መንበረ ማርያም ገልጻለች። ያ በሕልሟ ሲያባርራት ያየችው ጥቁር ሰው እርኩሰ መንፈሰ እንደሆነና ሕፃኑ ደግሞ መድኃኔዓለም ሆኖ እንዳዳናት አምና ተርጉማዋለች።

መንበረ ማርያም ስለተደረገላት ድንቅ ተአምር ስኔ 10 እና 21 ቀን 2001 ዓ.ም የእመቤታችን ክብረ በዓል ዕለት በቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ቤተክርስቲያን በመድረክ ላይ ወጥታ ለሕዝበ ክርስቲያኑ መሰክራለች።

በመጨረሻ ያነሣንላት ጥያቄ «የተደረገልሽን ተአምር እንዴት ትገልጭዋለሽ?» ነበር። እሷም «እግዚአብሔር ያደረገልኝን ድንቅ ተአምር በቃላት ልገልጸው አልችልም። ኃያሉ እግዚአብሔር እኔን አድኖኛል ምስጋና ይድረሰው። እኔ ግን የማተኩረው ስለተደረገልኝ ተአምር መመሰከር ብቻ ሳይሆን ስለማሰተላለፈው ነገር ነው። ይኽም እግዚአብሔር እንዲህ ማዳን እየቻለ ስይጣን ሊሰለጥንብን አይገባም። በሥራ፣ በትምህርት ቤትና በዕለት ተዕለት ሥራችን ላይ ውጤታማ እንዳንሆን መሰናከል እየሆነ ነው። ሕይወታችንን እያበላሸ መሆኑን አልተረዳንም። ስለዚህ ሰመ ክርስትና ብቻ ይዘን መቀመጥ ሳይሆን በጸም በጸሎት እግዚአብሔርን ማገልገል ይኖርብናል። ከንስሓ አባት ጀምሮ የሃይማኖት አባቶችም ማሰተማር አለባቸው። እያንዳንዱ ሰው ራሱን ይመርምር፤ ክፉ መንፈሰን መዋጋት አለበት» ብላለች።

«ማየት ማመን ነው» እንደተባለው በወቅቱ በደብረ ወልደ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንሰና በመካነ ጎለጎታ ቅድስት ማርያም የጠበል ቦታ ሲያጠምቋት የነበሩትና ድርጊቱን የተመለከቱት ሊቀ ትጉኃን ሰሙር አሐዱ ስለሁኔታው እንዲነግሩን ጠይቀናቸው እሳቸውም ታሪኩን እንዲህ አወጉን። «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም፤ ነገሩ ተአምር ነው። ከዚህ በፊት በእርኩሰ መንፈሰ የታሰሩ፣ የተተበተቡ ሰዎችን በእግዚአብሔር ኃያልነትና መሰቀል በመታገዝ በላያቸው ያለውን አጋንንት አሰለቅቄያለሁ። ይህ ግን ልዩና በሕይወቴም ገጥሞኝ የማያውቅ ነው። በዕለቱ እኅታችን መንበረ ማርያም ወደምትጠመቅበት ክፍል ስትገባ ጀምሮ በጣም ትጮሃለች። በመሰቀል እያጠመቅሁ ምንድን ነህ? ስለው አጋንንት ነን አሉ፡ ቀጥሎ ሰንትናችሁ? አልኩት 600 አጋንንት ነን አሉና እውነቱን አውጣ ብዬ አጥብቄ ሰይዘው 680 ብሎ ለፈለፈ። መጨረሻ ላይ 681ኛ ተልከሰካሽ የዛር መንፈሰ እንዳለ ገልጾ ከስኔ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ በተከታታይ በእራት ቀናት ውሰጥ ተከፋፍሎ ወጣ» ብለዋል።

እንደ እሳቸው አባባል ስኔ 10 ቀን 2001 ዓ.ም 80ው ጥቁር ወፍ ሆኖ ሲወጣ፤ በነጋታው «593ቱ ጉን ዳን ሆኜ እወጣለሁ» ብሎ ጮኸ፤ ሲለቅ ወዲያውኑ ከየት መጣ ሳይባል አካባቢውን ጉንዳን ወረረው። በሦስተኛው ቀን ደግሞ ሰባት ሲወጣ ከሰባቱ አንዷ ብቻ ሴት ሆና ተገኘች። እሷም «ከውጭ ሀገር ነው የመጣነው፤ ሥራችን ተመሳሳይ ፆታዎችን ማጋባት ሲሆን በውጭው ዓለም አጥለቅልቀነው ወደ አፍሪካና ኢትዮጵያ በብዙት እየገባን ነው» ብላ ተናግራለች።

«በመጀመሪያ ዋናውና አለቃው ' አጋንንት ጥቁር ወፍ ሆኖ ሲወጣ 600ው ሠራዊት ነኝ ብሎ ወጣ። አለ ቃውን አጋንንት» እንዴት ብለህ ነው የምትወጣው» ስለው እንደ አንበሳ አጓርቼ እወጣለሁ አለ። ልጅቷ እንደ አንበሳ እያጓራች ሳለ ጥቁር ወፍ በደም ተለውሶ ከሆዷ ውሰጥ በአፏ ወጣ፤ ሲወጣም ልክ እንደ አየር ሞገድ ተወርውሮ ገጓዳ ነገር ላይ አረፈ። ይህ እርኩሰ መንፈሰ ወፍ ሆኖ ሲወጣም ግፊት ስለነበረው እኔን ሁሉ ገፍትሮኛል። የወጣው ጥቁር ወፍ ከነሕይወቱ በመሆኑ ለተወሰነ ደቂቃ የማሰካካት ድምፅ አሰምቷል። ለግማሽ ሰዓት ያህልም በሕይወት ቆይቶ ምእመናን ዐይተውታል። ድርጊቱ የሁሉንም መንገደኛ ቀልብ የሳበ ስለነበር መናፍቆች ሳይቀሩ ተመልክተው በእመቤታችን ድንቅ ተአምር ተገርመ ዋል። በተለይ እንድ ከነቀምት የመጣ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ በተአምሩ ተደንቆ ሲያለቅስ ዐይቻለሁ» በማለት ሊቀ ትጉኃን ሰሙር አስረድተዋል።

«አጋንንቱ መንበረ ማርያምን እንዴት እንደያዙት ሰጠይቀው በተለያየ ምክንያት በይበልጥ በዛር ውላጅ ሲወርድ ሲዋረድ በዘር ሐረግ የመጣ እንደሆነ ለፍልፏል። ለ20 ዓመታት ያህል በሆዷና በማሕፀኗ ላይ ከፍተኛ ጫና በማድረስ ያስቃያት

እንደነበር ዘርዝሯል። በወር አበባዋ ጊዜ ምጥ እያበዛ ያስቃያት እንደነበር ተናግሯል። እመቤቴ፣ እመቤቴ እያለች የእመቤታችን ማርያምን ስም እየጠራች አስቸገረችኝ እንጂ ሆዷን ኦፕራሲዮን አስደርጌ በሰበብ ልገድላት ነበር» ሲልም ተናግሯል ይላሉ፡

«ድርጊቱ በጣም የሚከብድ እና በእኔ ላይ የደረሰ ያህል ተሰማኝ፤ እኔም በሁኔታው በጣም ያዘንኩበትና ያለቀስኩበት ነው። ምክንያቱም ይህ ድርጊት በእኔ ላይ ተከሰቶ ቢሆን ኖሮ ምን ልሆን እንደምችል ትንሽ ቆም ብዬ ማሰብ ጀመርኩ፡ እሷ ግን እጅግ በጣም ጠንካራ፣ በእምነቷ ጽኑ ነች። በእምነቷ ጽናት እግዚአብሔር ድንቅ ሥራውን ሠራላት። አሁን ሙሉ ለሙሉ ጤነኛ ነች ብለዋል። እርኩሰ መንፈሱ አባቷን ሳይቀር ሌሎች ሰዎችንም ይዣለሁ ብሎ በመለፍለፍ ልጅቷ ቤት ድረስ በመሔድ መጥተው እንዲጠመቁ ተናግሬያለሁ» በማለት ሊቀ ትጉኃን ተናግረዋል።

በመጨረሻም «የማስተላልፈው መልእክት አለ። እግዚአብሔር ብዙ ሥራ ይሠራል፤ እግዚአብሔር እኛ እንድንድን የማያደርግልን ነገር የለም። ከዚች እኅት ትልቅ ትምህርት አግኝተንበታል፤ የክርስቶስ ሰልጣን ይህን ዐይነት የሚሠራ ከሆነ እኛ የት ነን? ብለን ማሰብ አለብን። ትንሽም ብትሆን እምነት ያስፈልጋል። ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ጠበሉን፣ እምነቱን ልንጠጣ ይገባል፤ ሥጋና ደሙን ልንቀበል ያስፈልጋል። ይህ ከሆነ መዳን እንዳለ ማመን ይገባል» ሲሉ ሊቀ ትጉኃን ሰሙር አሐዱ አስረድተዋል።

በርግጥም መንበረ ማርያምና አጥማቂዋ ሊቀ ትጉኃን እንደገለጡት በየጠበሉ ቦታ ሲታይ በርኩሰ መንፈስ በመተት፣ በዛር፣ በአጋንንትና በመሳሰሉት የተያዙ ሰዎች በእግዚአብሔር ኃይል ሲፈወሱ ማየት ጉድ ያስኛል። ስይጣን የምንፈራው ሳይሆን ታግለን የምናሸንፈው መሆኑን ማንም ሰው ሊያውቀውና ሊረዳው ይገባል። አውቆም በጸም በጸሎት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል። የበለጠ ደግሞ መምህራን ሓላፊነት ወስደው ማስተማር ይኖርባቸዋል።